# <u>አቶ ስየ አብረሃ በመቀሌ ያደረጉት ንግግር</u>

**የተከበራችሁ የመቀሌ ከተማ ነዋሪዎች**

ከበርካታ ዓመታት በኋላ ከፊታችሁ ቆሜ ለመናገር በመብቃቴ የተሰማኝን ጥልቅ ደስታ ልገልፅላችሁ እወዳለሁ፡፡

ከሁሉ አስቀድሜ ለዚህ ላበቃኝ ፈጣሪ ክብር ምስጋና ይድረሰው እላለሁ። በመቀጠል ላለፉት ዓመታት በእኔና በቤተሰቤ ላይ የተፈፀመብንን ግፍ በማሰብ ላዘናችሁ፣ ከዚያም ባሻገር የግፍ እርምጃዎችን በመቃወም አንዲት ቃልም ብትሆን ለተነፈሳችሁ ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ዛሬ ከፊታችሁ ለመቆም አጋጣሚውን በማግኘቴ ከእኔ ለመስማት የምትፈልጉት ብዙ ነገር፣ ለእኔ የምትቀርቧቸው በርካታ ጥያቄዎች እንደሚኖሩ እገምታለሁ፡፡ እንደኔ እንደኔ ያለፈው አልፏል በማለት ወደፊት 'እንዴት እንሂድ' በሚለው ጥያቄ ላይ ለማተኮር በመረጥኩ። ሆኖም ያለፈውን ሳያነሱ የወደፊቱን ለመመልከትና ለማመላከት መሞከር የራሱ ችግር ይኖረዋል። በመሆኑም ወደኋላ መለስ እያልኩ አንዳንድ ነገሮችን ማንሳቴ ባይቀርም ዋናው ትኩረቴ ዛሬ ለመገናኘት ዋነኛ ምክንያት በሆነው ጉዳይ ከበኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ጋር የመተዋወቅ ጉዳይ ላይ ይሆናል። ለነገሩ ያለፈውን አንስተን እንወያይ ቢባልስንኳ በአንድ ቀን ያውም ጥቂት ደቂቃዎች በሚፈጅ ንግግር አማካይነት በቂ ማብራሪያ ለመስጠት እንደማይቻል እናንተም ታውቁታላችሁ፡፡

ዛሬ እንኳን በሰላም አገናኘን በማለት የተጠቀምኩበትን ይህን አጋጣሚ የፈጠረልኝ መድረክ በሚባል የሚታወቀው ድርጅት ነው ።

ከእናንተ ፣ከአባቶቻችሁ፣ ከእህቶቻችሁና ከወንድሞቻችሁ ጋር ያካሄድነው የትጥቅ ትግል አፋኙን የደርግ ስርአት በማስወገድ በድል መጠናቀቁ ይታወቃል፡፡ደርግን ብናስወግድም የተነሳንባቸው የትግሉ ዓላማዎች ሙሉ በሙሉ የታለመላቸውን ግብ አለመምታታቸው ግን ይታወቃል፡፡

ዛሬ የተገናኘነውም የትጥቅ ትግሉን ተከትሎ መምጣት የነበረበትን እና ሳይመጣ የቀረውን እናሳካ ዘንድ ለሰላማዊ የፖለቲካ ፉክክር አመቺ የሆነ ሜዳ እንዲፈጠርና በዝያውም የተነሳንለትን አላማ እንድትደግፉ ለመጠየቅ ነው፡፡

በዚያ ትግል ሂደት ውስጥ አልፈን በህይወት የምንገኝ ወገኖች የየድርሻችንን ያበረከትን ቢሆንም ከቋሚው ይልቅ የበለጠ ዋጋ የከፈሉትና የበለጠ ክብር የሚገባቸው የአካል መጉደልና በተለይም የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉት ታጋዮች ናቸው፡፡ የተከፈለው መስዋዕትነት ከንቱ ላለመቅረቱ ዋነኛ መለኪያ ቢኖር እነሱ የወደቁለትን ዓላማ በመተግበር አደራቸውን አክብሮ መፈፀም ነው፡፤ (ከዚህም ጎን ለጎን በትግሉ ወቅት አካላቸው ለጎደለ እንዲሁም የሟች ቤተሰብ ለሆኑ ወገኖች አስፈላጊውን እንክብካቤ ማድረግ ለቋሚው ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው አያጠራጥርም፡፡)

ይህን አላፊነት ወደ ጎን በመተው በአንድ በኩል በስማቸው እየዘመሩ፣ እየማሉና እየተገዘቱ በሌላ በኩል ደግሞ በህይወት ስለተቆዬ ብቻ ራስን የትግሉ (ብቸኛ ባለመብት ወይም) አድራጊ ፈጣሪ አድርጎ በማቅረብ በህወሃት ባለስልጣኖች የሚደረገው የታሪክ ስርቆት እሽቅድምድሞሽ የለየለት የክህደት መንገድ መሆኑን ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡

ከትግሉ ዓላማዎች አንዱ የፖለቲካ ስልጣን መያዝ የነበረ ቢሆንም በትግሉ ወቅት የነበረን ዓላማ ደርግን ጥሎ ስልጣን መቆጣጠር ብቻ አልነበረም፤

- ዜጎች ያለ ስጋት በሙሉ ነፃነት ተገቢውን ሰብዓዊ ክብር እንዲጎናጸፉ ማድረግም የትግሉ አላማ ነበር፤
- የህዝቦቿ እኩልነት የተረጋገጠበትና ሉአላዊነቷ የተጠበቀ አገር ለትውልድ ማውረስም የትግሉ ዓላማ ነበር፤
- እውነትና ፍትህ የሚከበርበት ስርዓት ለመዘርጋት የተደረገ ትግልም ነበር፤
- ድህነትና የምግብ ርዳታ ቀርቶ ራሳችንን የምንመግብበትና ሰፊ ልማትን ለማምጣት የሚያስችለንን ስርዓት መዘርጋትም የትግሉ ኣላማ ነበር፤
- ከኤርትራ ጋር የሚኖረንን ዝምድና በሚመለከትም ችግሩ ተፈትቶ ቢያንስ ሰላምን አግኝተን መኖር ምኞታችን ነበር፡፡

እነዚህን ፍላጎቶችና ዓላማዎች በትግሉ ወቅት ይዘናቸው የነበሩ ቢሆኑም አንዳንድ እንከኖችንና ችግሮችንም ጭምር የያዙ እንደነበሩ አይካድም፡፡ ሆኖም በሂደት እየተማሩ በማስተካከልና ሂደቱን ለማቃናት የሚያስችል ሰፊ ዕድል ነበር። በዚያ መሰረት የተተገበሩ የማስተካከያ እርምጃዎች እንደነበሩም ይታወቃል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ጉድለቶችን እየተመለከተም ቢሆን የእርምት እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል ትዕግስት አሳይቷል፤ እድልም ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ህወሃት ትዕግስቱን በማክበር በዕድሉ ለመጠቀም ባለመቻሉ የታለመው አልተገኘም፤ ማሻሻልና ማረሙ ቀርቶ የነበሩት ጥቂት አዎንታዊ ጅምሮችም ተቋርጠው ቀርተዋል፡፡

የኤርትራን ችግር ለመፍታት ህወሃት ከጅምሩ የተከተለው መንገድ ከችግር ያልፀዳ እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡ ተፈጥሮልን የነበረው ችግሩን ለማረም የሚያስችል አጋጣሚ ሊያመልጠን በመቻሉም ወደባሰ ማጥ ተዘፍቀናል። አገራችን ወደብ አልባ ሆና መቅረቷ ሳያንስ እንደገና ወደ ጦርነት ለመግባት ተገደናል። ጦርነቱ ካልቀረልንም አንደኛችንን ጉዳያችንን ጨርሰን መውጣት ስንችል አሁንም መቋጫ ወደሌለው ችግር ውስጥ ገብተናል። ሰራዊታችን አላረፈም። አሁንም ምሽግ ውስጥ ነው። የትግራይም ክልል በኢትዮጵያ ውስጥ ለኢንቨስትመንት ከማይመረጡ ያልተረጋጉ አካባቢዎች አንዱ ሆኖ ይገኛል፡፡ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ውስጥ ትግራይ ውስጥ በፋብሪካዎች ፋንታ የጦር ሰፈሮች ቁጥር መጨመሩም የችግራችንን ክብደት ያመለክታል፡፡

እጅግ የሚያሳዝነው እውነታም ያ ለፍትህና ለዲሞክራሲ ብዙ ዋጋ የከፈለው ህዝብ የጥቃት ዒላማ እንዲሆን መደረጉ ነው። ለፍትህና ለዲሞክራሲ የሚደረግን ትግል ከሻዕቢያ ጋር በማስተሳሰር ለማጥላላት የሚደረገው ፓለቲካዊ ጥረትም የዚህ አንዱ አብነት ነው፡፡

የሻዕቢያ ወረራ ዱብ ዕዳ ነበር፡፡ ሆኖም ለጉዳዩ የማያዳግም መቋጫ ለማድረግ የሚያስችል ዕድል ፈጥሮልን ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ከ 1991 ዓ.ም ጀምሮ የተፈጠረው ልዩነት ነሐሴ 1991 ዓ.ም በተካሄደው የማ/ኮ ስብሰባ የተፈጠረውን ልዩነት በውይይት ለማስተካከል ተወስኖ የነበረ ቢሆንም በጦርነት መሃል ይህንን ችግር ለመፍታት እንቀመጥ ዘንድ ሁኔታዎች አይፈቅዱም በማለት ነገሩን አቆይተን ስናበቃ ጦርነቱ መቋጫ ከተበጀተለት በኋላ በ1993 ዓ.ም ስብሰባ ተቀምጠን ነበር። የልዩነታችን መንስኤ ሉአላዊነትና የአገር ጉዳይ ሆኖ ሳለ በውይይቱ ሂደት የሙስናና የዲሞክራሲ አጀንዳን በመሰንቀር የትኩረት አቅጣጫን የማስቀየር ዘዴ ተቀይሶ ነበር፡፡ ሙስና ትኩረት ሊሰጠው ይገባል የሚል እውነተኛ አቋም ካላችሁ እንግዲህ

የሁላችንም (ንብረት) ይዞታ እንዲፈተሽ ሀሳብ አቀረብን። ይሄኔ ሃሳቡ የጸረ-ሙስናውን ትግል ለማደናቀፍ የተሰነዘረ ነው አሉን፡፡
ልዩነቱን ይፈታል ተብሎ የተጠራው የማ/ኮ ስብሰባ ችግር ውስጥ ሲገባም ጉባኤ ይጠራና አቋማችንን ይዘን እንቅረብ ማለታችን ወንጀል ሆኖ 'ጉባኤ እስኪጠራ ድረስ ከኃላፊነታችሁ ታግዳችኋል' የሚል ቀላጤ ደረሰን። በዚያውም ከድርጅቱና ከመንግስት ኃላፊነት አስወጡን። አንዳንዶቻችን ደግሞ ከመላው ቤተሰባችን ጋር ወህኒ አወረዱን። ራሳችንን ለመከላከል በማንችልበት ሁኔታ ውስጥ አስቀምጠውን ሲያበቁ ስማችንን ለማጥፋት ለበርካታ አመታት ሲጥሩ ቆይተዋል፡፡ ሆኖም ውሸትና ስንቅ እያደር ይቀልላል እንዲሉ ያ ሁሉ የሙስና ወሬ እንደ ጉም ተበትኖ ደብዛው ጠፍቶ ቀርቷል።

ሃብታችን (ይቆጠር) ይፈተሽ ያልነውም ሆነ አንፈተሽም ያሉት በምን ዓይነት ሁኔታ እንደምንገኝ አገር የሚያየውና የሚያውቀው ፣ ፀሃይ የሞቀው እውነታ በመሆኑ፤ አሁን በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ለማለት አልፈልግም። እዚህ ላይ ልብ እንድትሉት የምሻው ዋነኛ ጉዳይ ህወሃት ልዩነቶችን የሚፈታበት ስትራቴጂና ስልት በአገራችን ሰላምም ሆነ በድርጅቱ ህልውና ላይ የሚያስከትለውን አደጋ ነው፡፡

## ከቡራንና ከቡራት

የህውሃት ፖሊሲዎችና ልዩነቶችን የሚፈታባቸው ዘዴዎች የማታ ማታ ለአገራችንም ሆነ ለትግራይ ህዝብ ምን ትርፍ እንደሚያስገኝ ቆም  ብለን ለመመርመር የምንገደድበት ደረጃ ላይ መድረሳችንን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ህወሃት በአንድ በኩል ለህገ መንግስቱ ተገዢ መሆኑንና በዚያም እንደሚመራ፤ በሌላ በኩል አብዮታዊ ዲሞክራሲን እንደሚከተልና በዚያም እንደሚመራ ይገልፃል። ታዲያ የአብዮታዊ ዲሞክራሲን መርህ በህገ መንግስቱ ሰፍረው ከሚገኙ መርሆች ጋር የሚጋጭ ነው፡፡
አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ በተፈጥሮው የመድብለ ፓርቲ ፅንስ ሃሳብን አይቀበልም።አብዮታዊ ዲሞክራሲ አንድን የፖለቲካ መስመር፣ አንድ ፓርቲ ሁሉን ሊመራና ሊቆጣጠር ይገባዋል የሚል አስተሳሰብ ያራምዳል፡፡ ከዚህም በመነሳት የፖለቲካ ፓርቲዎች ህልውናና አቋሞቻቸው፣ የህ/ሰቡ ነፃ ድርጅት ድምፆች ህልውና፣ሁሉንም ዜጎች በእኩልነት ዓይን የሚመለከቱና የሚያገለግሉ መንግስታዊ ተቋሞችን ህልውና አይቀበልም። ሁሉም በመሪ ፓረቲውና በአቋሞቹ ቁጥጥር ስር መዋል አለበት። ይህም በህገ መንግስቱ ውስጥ ከሰፈሩት መርሆች ጋር በቀጥታ የሚጋጭ አቋም ነው፡፡

የህወሃት ሊቀመንበር በዘንድሮው የየካቲት 11 በዓል ላይ ያቀረበው ንግግርም ከዚህ መርህ የሚመነጭ ነው፡፡ የትግራይ ህዝብ ሁሉም አማራጮች ቀርበውለት የሚመርጠውን እንዲደግፍ አልተፈለገም። ህዝቡ ህወሃት የሚመረጥለትን ብቻ እንዲመርጥ ነው የሚፈለገው። በእኛ እምነት ስንዴውን ከገለባው መለየት ያለበት ህዝብ ብቻ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ይኖር ዘንድ እንቅፋቶች በሙሉ ሲጠረጉ ህዝቡ ያለ ምንም ጥርጣሬና ፍርሀት ፍላጎቱን ለማንጸባረቅ ሲችል ነው፡፡

ለህወሃት መሪዎች የምናቀርብላቸው መልዕክት አንድና ግልጽ ነው፤ የናንተማ ፍርድ ከዛሬ ስምንት ዓመት ጀምረን አውቀነዋል፤ታስረን ተገርፈንበትም በፅናት ተቋቁመን በመቆም እዚህ ደርሰናል (ለዚህ በቅተናል)፡፡ አሁን ደግሞ በተራው ሕዝቡ ፍርዱን እንዲሰጥ ሁኔታዎችን አመቻቹለት፤ ፍርዱ የህዝብ መሆኑን ተቀበሉ እንላቸዋለን፡፡ በአንድ እጅ አብዮታዊ

ዲሞክራሲ በሌላኛውም ህገመንግስቱን ይዛችሁ ሳይሆን በህገመንግስቱ እንደተደነገገው ከፍርሀትና አድልዎ ነፃ ለሆነ ምርጫ ቁሙ ነው የምንለው፡፡

አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሰፊ አድማስ የሚሸፍን ሁለንትናዊ ልማትን አይቀበልም። እርሻ መር የኢንዱስትሪ ልማት እከተላለሁ በሚል ኢንዱስትሪን ጨምሮ ሌሎቹን (የኢኮኖሚ) ዘርፎች አምክኗቸው ይገኛል፡፡ እርሻውም ቢሆን ኢንዱስትሪውን ሊመራ ቀርቶ ራሱንም ካለበት ሊያንቀሳቅስ አልቻለም። አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሌሎቹን (የኢኮኖሚ) ዘርፎች ጨምድዶ መያዙ ሳይበቃው ባለሃብቱንም ጭምር ጨምድዶ በመያዝ አሽከር ሊሆንለት የሚችል ባለሃብት ለመፍጠር በጥረት ላይ ነው። ኪራይ ሰብሳቢ እና ልማታዊ በማለት ባለሃብቱን መለያየት የተፈለገበት ምክንያት ይኸው ነው፡፡ አብዮታዊ ዲሞክራሲ አንዱን ፓርቲ ብቸኛ ገዢ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ፓርቲው ራሱ ባለሃብት እንዲሆን በማድረግ ግለሰብ ባለሃብቱን ለማክሰም የሚያልም መስመር ነው፡፡ በገበሬው ላይ ገዢ፣ ዘመናዊ ጉልተኛና አበዳሪ በመሆን ሁሌም ጥገኛው በማድረግ የሚያኖር የፖለቲካ መስመር ነው፡፡

ይህ አካሄድ በልማት ወደፊት ሊያራምድ ቀርቶ የነበረውን ሂደት እስከማጨናገፍ ደርሷል። የትግራይንም (የልማት) ሁኔታ ብንመለከት ተሃድሶ ከተባለው ተረት ተረት ወዲህ የተሰራውን ከዚያ በፊት ከተሰራው ጋር ብናነፃፅር ሰማይና መሬት ነው፡፡ ድሮ ከነበረው እርምጃ ጋር በሚጠጋ መጠን ሊጨምር ቀርቶ በዚያን ጊዜ በጋራ የታቀደውንና የተጀመረውን የሚያጨናግፍ ስራ ነው የተሰራው፡፡ በመስኖ ላይ የተሰራው በምግብ ራስን የማስቻል ዕቅድ ለመተግበር ሳርት የተባለ ድርጅት ተቋቁሞ የራያን መስክ ለማልማት ትልቅ ሥራ ተጀምሮ ነበር። እነዚህም ለድሃው ገበሬ የሚጠቅሙና ገበሬውን ማዕከል ያደረጉ ዕቅዶች ነበሩ፡፡

በርካታ ምሁራንና ባለሙያዎች የተሳተፉበት ገበሬውን በምግብ እህል ራሱን ያስችሉታል የተባሉ ትላልቅ ዕቅዶች ነበሩ። እነዚህም ተጨናግፈው እንዲቀሩ ከተደረጉት ዕቅዶች የሚጠቀሱ ናቸው። በእነዚህ ፈንታ **ተሐድሶ** ለገበሬው ያቀረበለት አማራጭ ትንሽ ስራ ሰርቶ ላዩ ላይ ላስቲክ በማንጠፍ ውኃ ማቆር ነው፡፡ የራያ ገበሬ በአፄ ኃይለስላሴ መንግስት (ጊዜ) መሬቱን ተቀምቶ ለጭሰኝነት መዳረጉ የሚታወስ ነው፡፡ **ተሓድሶው** ለራያ ገበሬ ያቀረበለት አማራጭ ያለማውን መሬቱን ለግል ባለሃብቶች በመስጠት ገበሬውን ወዲያ መግፋት ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህም ወደ ዘመናዊ ጭሰኝነት የሚመልስ አማራጭ ነው፡፡ **ተሃድሶው** ይህንን ልምድ ወደ ሌሎች አካባቢዎች ሊያስፋፋው እንደሚችል የሚጠቁሙ ምልክቶች ይታያሉ፡፡

አንዴ ከሶስት ዓመታት፣ ሌላ ጊዜ ከአምስት ዓመታት በኋላ በምግብ እህል ራሳችንን እንችላለን የሚሉ ስለቶች ቢገቡልንም ፓርቲው በሚከተለው የተሳሳተ ፖሊሲና አካሄድ ምክንያት ህዝባችን አሁንም በምፅዋት እህል እንደቆመ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በህዝቡ ስም ተለምኖ የሚመጣው የምፅዋት እህልም ቢሆን ፖለቲካዊ አድልዎ እየተፈፀመበት የሰዎችን ሀሳብ የመግለፅ ነፃነት ለማፈን ጥቅም ላይ እየዋለ ነው፡፡ የደርግን ስርዓት የታገለን ህዝብ በድህነቱና በችግሩ በኩል በመግባት ለማንበርከክና ዓፈናን የመታገል ባህሉን ለመስበር በመሳሪያነት እያገለገለ ይገኛል፡፡

### ከቡራንና ከቡራት

አስራ ሰባት ዓመታትን በፈጀውና ከባድ መስዋዕትነትን ካስከፈለው ትግል በኋላ የትግራይ ህዝብ ተስፋና ምኞት ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ውንድሞቹ ጋር በዚህች አገር ውስጥ ያለምንም ስጋት በፍቅር የሚኖርበት፣ እንዲሁም የአገሩ የልማትና ዕድገት አካል በመሆን መብቶቹና ክብሩ ተጠብቆለት ሊኖር የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ነበር። ከነበረው የደርግ ግፍና የጭፈና ዘመን በትግሉ መላቀቅ መቻሉ አንዱ አብይ ጸጋ ነው፡፡ ሆኖም ስጋቱ አልጠፋለትም። ትግራይዋይ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል

ውስጥ  ለመኖርና ሰርቶ ኑሮውን ለመግፋት የሚያስችል ሁኔታ አልተፈጠረለትም።ሳይበላ እንደበላ ይቆጠራል። እንደሰው በማንነቱ ሳይሆን በስልጣን ላይ ከሚገኙ ገዢዎች ጋር በጅምላ ይታያል፡፡

በትግራይዋይ ላይ ያለውን የጥርጣሬና የማግለል መንፈስ ዋነኛ ፈጣሪው የህውሃትና ጓዶቹ የሚላቸው የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የሚያራምዷቸው ፖሊሲዎች መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል፡፡
የኢትዮጵያን ህዝብ በሙሉ ሊያስተሳስር የሚችል ፖሊሲ ለማምጣት አልቻሉም። የቆየውን ቁስል እያከሙ ሰዉ በአንድነት እንዲተቃቀፍና እንዲቀራረብ በማድረግ ፈንታ የቆየውን ቁስል እያጋነኑና ልዩነቶችን እያራገቡ ብሔር ብሔረሰቦች እርስ በእርስ በጥርጣሬ ዓይን እንዲተያዩ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ህዝቡ በአንድነት ሲነሳባቸው ደግሞ ትግራዋዩን በህውሃት፣ ኦሮሞውን በኦህዴድ ወዘተ  በመግባት ስሜቶቹንም እየቀሰቀሱ ሲለያዩት ቆይተዋል፡፡ በዚህም አማካይነት ኢትዮጵያውያን የጋራ ጉዳዮቻቸውን በአንድነት ለማየት የማይችሉበትን ሁኔታ ተፈጥረዋል። በትግራዋዩ እየታየ ያለው በጥርጣሬ ዓይን የመታየት አዝማምያ ኦሮሞውን፣ አማራውን፣ ሶማሌውን፣ ሲዳማውን፣ ጋማቤላውን እና ሌሎች የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ላይ እያጋጠመ ያለ ችግር ነው፡፡ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በኢትዮጵያዊያን መካከል በአንድነት ፋንታ ከመጠን ያለፈ ጥርጣሬና የአንድነታችንን መዳከም ፈጥሮ ይገኛል፡፡

ለችግሩ መፈጠር አንዳንድ የተቋዋሚ ፓርቲዎች የራሳቸው ድርሻ እንደነበራቸው ይታወቃል፡፡ እነደምሳሌ ለማውሳትም ያክል በምርጫ 97 **ትግራዋይን** ከህወሃት ለይቶ የማያይ ቅስቀሳ ነበር፡፡ አገራዊ ቁምነገሮችንና ወንድማማችነትን በማስተማር ፈንታ ትግራዋዩን የፖለቲካቸው መለማመጃ ያደረጉ ፖለቲከኞች ታይተው ነበር፡፡ ይሁንና በዋነኛነት ይህን የመሰለውን የጥላቻ ነቀርሳ የፈጠረው የገዢው ፓርቲ ፖለቲካ መሆኑ ከቶ መዘንጋት የለበትም፡፡ ገዢው ፖለቲካም የህወሃት/ኢህአዴግ አብዮታዊ ዲሞክራሲ መርህና የብሄር ፖለቲካን ማዕከል ያደረገው ፖለቲካው መሆኑ ከቶ ሊዘነጋ አይገባውም፡፡

የህወሃት መሪዎች የራሳቸውን ችግሮች እንደመመልከት ችግሩን በተቃዋሚዎች ላይ ይለጥፉታል፡፡ ይህንንም እምነታቸውን በትግራይ ህዝብ አዕምሮ ውስጥ ለማስረፅ ከፍተኛ ጥረት እንደሚያደርጉ ይታወቃል፡፡ ስህተቶቹ ቢመዘኑ በስልጣን ላይ ያሉት የህወሃትና የጓዶቹ ድርሻ የበለጠ እንደሚሆን መገንዘብ ይገባል፡፡ እነሱ ለፍትህ፣ ለፍቅርና ለአንድነት ተግተው ቢሰሩ ኖሮ ችግሩ እንዲህ ባልገዘፈ ነበር፡፡

**ከቡራንና ከቡራት**
'ህወሃት' ተሰኝተን ትግል ስንጀምር እናርመዋለን ብለን የተነሳንለት የዚህች አገር ችግር እንደፍላጎታችንና እንደተመኘነው አልፈታነውም፡፡ አሁንም ችግሩ ውስጥ እንገኛለን፡፡ የድሮው ስጋታችን መልኩን ከመቀየሩ በቀር አልጠፋም፡፡ ህዝባችን በተለይም ትግራዋይ ፍትህ ማጣቱና፣ ከድህነቱ የሚወጣበት መንገድ የሚታየው አለመሆኑ በተጨባጭ የሚታይ እውነታ ነው፡፡
ሆኖም ይህን ለመለወጥ በሚደረግ ትግል ውስጥ በትጋት ያለመሳተፍ አዝማሚያ ይታያል፡፡ በመሃል አገር የሚታዩትን የፍትህና የለውጥ ፍላጎቶች በተስፋ ሳይሆን በስጋትና በጥርጣሬ ሲመለከት ይታያል፡፡

ህውሀት ሕዝብን ከጥቃት በመታገድ ፈንታ በማቃለል ስራ ለይ ከተጠመዱት ጓዶች ጋር የተመሰረተውን ሽርክና እንደቅዱስ ነገር በማቅረብ ሌሎቻችን ከመሰል ኢትዮያውያን ድርጅት ጋር የምንፈጥረውን የማቀራረብ ግንኙነት ግን ከጠላት ጋር የተደረገ መቀርረብ ተደርጎ በማስመሰል ለማንቋሸሽ ይሞክራል፡፡

ኤርትራን በሚመለከት ሲከተለው የቆየውን እስከአሁን ሰላምን ያላመጣውን ፖሊስ በጤነኛ መንፈስ ገምግሞ ከማቃናት ፈንታ የኢትዮጵያ ባህር በር የማግኘት ተፈጥሮአዊ፣ ታሪካዊና ህጋዊ መብት አላት የሚሉትን ወገኖች በአንድ በኩል እንደ ዘረኞች ሲያቀርብ በሌላ በኩል.... የሻቢያ ሽርኮች ናቸው በማለት አስነዋሪ ጥላሸት ይቀባቸዋል፡፡ በዚህ ክስ ውስጥ የህውሀትና የኢህአዴግ መሪዎች የነበረውንም ጭምር ያስገባናል፡፡በጣም ያስገርማል፡፡

- እንዲህ አይነት አካሄድ በጸብና ስጋት ውስጥ በቀጣይነት የሚኖር እንጂ ከዚያ የማያስወጣ አይደለም፡፡ መፍትሄም በቸልታ መንገድ በመቀጠል ሳይሆን ቆም ብሎ ነገሮችን እንዳዲስ መመልከት ነው፡፡
- እኛ ያለነው መንገድ የእኛ አካሄድ ከልሆነ በቀር ሌላው መንገድ ሁሉ የጥፋት መንገድ ነው የሚለውን ሕውሀት ለረጅም ግዜ የዞት የቆየው አካሄድና አስተሳሰብ የትም አንደማያደርሰው (አንደማይሰራ) መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡
- የሀገር ጉዳይ የሁሉም ኢትዮጲያውያን ጉዳይ መሆኑን እንዲያ ግዙፍ የሆኑ ሀገራዊ አጀንዳዎች ህውሀትና ጓዶቹ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ፖለቲከኞችን የሚመለከቱና የሚያሳስቡ ጉዳዬች መሆናቸውን በመቀበል፣ ከሁሉም ጋር ተባብሮ በመሄድ ሀገራዊ መግባባትን በመፍጠሩ ብቻ የዚህን ሀገር ችግር ለመፍታት እንደሚቻል ሊታመንበት ይገባል፡፡
- ይህንን አለመቀበል በዚህ ችግር እኛ መድከማችን ሳያንሰን ቀጣዩ ትውልድ ችግሩን እንዲወርሰው ማድረግ ነው፡፡ መድረክን ያቋቋምንበት በመድረኩ ውስጥ የምንገኝ ፖለቲከኞች የተሰባሰብንበት ዋነኛው ምክንያት ይኸው ነው፡፡ የሚያሰባስቡን ሀገራዊ ጉዳዮች በውይይትና በጋራ መግባባት አማክይነት የጋራ መፍትሄ በማስቀመጥ በህብረት እንያቸው የሚል ዘመቻ ነው አሰባስቦን የሚገኘው፡፡ የህወሓትና ጓዶቹ መሪዎች መድረክ የኢትዮጲያን ውስብስብ ችግሮች የሚፈታበት ብቃት የለውም በማለት ቢመጻደቁም እኛ ይህንን አዲስ አካሄድ እንዲመጣ ምክንያት የሆነን ህውሀትና ጓዶቹ ከ 18 ዓመታት በኋላም ቢሆን ፈተናውን ለማለፍ አለመቻለቸውን በመገንዘናችን ነው፡፡ የማያዋጣው የእልህ መንገድ ተይዞ ከመደስኮር ይልቅ በምክክር ሁሉንም የሚያስማማ መፍትሄዎችና ፕሮግራም ይዞን መውጣት በመቻላችን ደግሞ ብስለትንና ሆደ ሰፊነትን የሚያመላክት ነው፡፡

ወደ ቀድሞው የአድልዎና የዐፈና ስርአት መመለስ የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ የለም፡፡ የታሪክ ሂደት ተሽሮ አልፎዋልና ፡፡ ከዚህም ባሻገር ህዝቦችን አሁን ባለው የህወሐትና/ኢህአዴግ አገዛዝ ስር መቆየት አይፈልግም። የኢትዮጵያ ህዝብ የለውጥ መለኪያው ሚዛኑ ያለፈው ስርዓት ወይም የአንድ አካባቢ ሁኔታ ባለመሆኑ ኢሳያስ ወይም መንግስቱ ማነፃፀርያ ሊሆኑት አይችሉም፡ ከእነዚህ እሻላለሁ እያለ የሚፎክር መንግስት አይፈልግም ። አሁን የሚፈልገው መንግስት የዓለም ማሕበረሰብ ተቀብሎ የሚመራባቸውንና አብዛኞቹ በአገራችን ሕገ መንግስት ሰፍረው የሚገኙትን መርሆዎች መሠረት በማድረግ ሃገር የሚመራ መንግስት ነው፡፡ በመድረክ ታቅፈን የምንገኝ ኢትዮጵያውያን መሰባሰብያችን ሃገር ወደ ተሻለውና በዓለም ማሕበረሰብ ተቀባይነት ባገኘው አቅጣጫ እንድትገሰግስ የማድረግ አላማ ነው፡፡

ህወሐት ይህን ለውጥ በስጋት ዓይን የሚመለከተው በመሆኑ የትግራይ ሕዝብን በስጋት እንዲመለከተው ለማድረግ ተግቶ እየሰራ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ስማችንን ለማጥፋት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡አመራሩ ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት የትግራይን ሕዝብ አስፈራርተው ሁሌም የእነርሱ መፈንጫ ማድረግ ስለሚፈልጉ ነው፡፡ ከእኛ በላይ ለትግራይ

ሕዝብ ስለሚያስቡለት አይደለም፡፡ በየትኛውም መመዘኛ እነርሱ ከእኛ በላይ ሊያስቡለት እንደማይችሉ ታሪካችንና ስራችን ምስክር ነው፡፡

እኛ ይዘነው ያለነው መንገድ የፍቅር የአንድነት የእርቅና ተስማምቶ የመኖር መንገድ ነው፡፡ ከዚህ መንገድ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተጠቃሚ ይሆናል ትግራይም ጭምር፡፡ የህወሓት አባላትም ቢሆን የሚጠቅማቸው ይኸው መንገድ እንጂ ያረጀው የፀብና የእልህ መንገድ አይደለም ፡፡ የትግራይ ተወላጆች የሆነው በዚህ መንገድ ብንሄድ ስማችን በክፉ ሳይነሳ ተከብረን በሰላም የምንኖርባት ሃገር ለልጆቻችን እናወርሳለን፡፡

የትግራይ ህዝብ ለሃገር ይበጃል ያለውን የራሱ ነፃ ኣቋም ይዞ ለመሄድ የሚችል ህወሃት በቀደደለት ብቻ የማይሄድ መሆኑ ለህወሃት መሪዎች ግልፅ መልእክት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ኣልፎ ተርፎ የህወሃት መሪዎች ወደ ትክክለኛው አገርን የሚጠቅምና የሚያድን መንገድ ይገቡ ዘንድ የትግራይ ህዝብ የራሱ ገንቢ ጫና ማሳረፍ ይጠበቅበታል፡፡ይህን በማድረግም ብዙ ጉዳት ሳይደርስ በፊት ነገሮች እነዲስተካከሉ ሊጠይቅ ይገባል፡፡በኛ በኩል ጉድለት ሲታየውም እነደዚሁ እናስተካክል ዘንድ ሊመከረን ይገባል፡፡

የህወሃት አባላትም ጎራ ለይቶ ከመራገም ወጥቶ ነገሮችን ከሀገር ጥቅም ከተተኪው ትውልድ ተስፋና እድል አኳያ ተመልክተው የራሳቸውን ገንቢ ሚና ሊጫወቱ ይገባል እንላለን ፡፡ እኛ ጠላቶች እንዳልሆን ልቦናችሁ ያውቃል፡፡ በቂም በቀልና በጥላቻ የምንመራ ሰዎች አይደለንም ከግላችን ስሜትና በደል የሚበልጥ ሃገራዊ ጉዳይ አለ፡፡ ይህ ተስተካክሎ ማየትን ከመፈለግ በቀር እንዲባባስ ለማድረግ ፍላጎት የለንም፡፡ ድርጅቱን ወደ ትክክለኛ መንገድ ለማስገባት በምትወስዱት እርምጃ ላይ ደግሞ እጥፍ ርቀት ተጉዘን ሃገራችን ወደ ትክክለኛ መስመር እንድትገባ ለማድረግ ዝግጁ መሆናችንን እንድትረዱልን እንፈልጋለን፡፡

በህወሓት/ኢህኣደግ ሰፈር ተቃዋሚዎች ስልጣን ከያዙ የሃገር መከላከያንና ሌሎች ተቋማት እንዲሁም የሲቪል ሰርቪሱን ያፈርሱታል፣ ሰራተኛውንም ያፈናቅሉታል እየተባለ ይወራል፡፡መከላከያ ሃይላችንም ሆነ ሁሉም ተቋሞቻችን ከአንድ ፓርቲ የስልጣን ዘመን ባሻገር አገራዊ ፋይዳ እንዳላቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ፓርቲዎች በተቀያየሩ ቁጥር የሚቀያየሩ መሆን አይገባቸውም፡፡በመሆኑም እነዚህ ተቋማት ከፖለቲካ ተጽእኖ ተላቀው ነፃ ተቋማት እንዲሆኑ፣ብሄራዊ ተዋፅኣቸውን በጠበቀ መልኩ ይበልጥ እንዲጠናከሩ መድረክ አበክሮ ይሰራል፡፡ መሰረታዊ እምነቱም ይህ ነው፡፡ ይህን እምነቱን ለማረጋገጥ የተቋማቱን ህልውና ቀጣይነትና ተኣማኒነታቸውን ለማጎልበት ማስተካከያዎችን ያደርጋል፡፡ መድረክ የጎበጡና የተበላሹ ነገሮችን ለማስተካከል የሚሰራ እንጂ ተቋማቱን የማፍረስ ይሁን የማናጋት ተልእኮም ፖሊሲም የለውም፡፡

የተከበራችሁ የትግራይ ወጣቶች

የእኔ ትውልድ የ60ዎቹና የ70ዎቹ ትውልድ ነው፡፡ የእናንተ ደግሞ የ21ኛ ክፍለ ዘመን ትውልድ ነው፡፡ የእኔን ትውልድ ያጋጠሙት ተግዳረቶችና የእናንተን ትውልድ የሚያጋጥሙት ተግዳረቶች ይለያያሉ፡፡ ከእኛ የምትማሩት ብዙ ነገር ይኖራል፡፡ሆኖም የኛዎቹ መፍትሄዎች ፈተናዎችን በሙሉ ለማለፍ የሚያስችሉ ብቸኛ አማራጮች ባለመሆናቸው ተጨማሪ መፍትሄዎችን ለማመነጨት ቁልፍ ሚና መጫወት ይገባችኋል፡፡

ኢትዮጵያዊያን ሴቶችና የኤሲያ ሴቶች ሁሉም ወደ አረብ ሀገሮች እንደሚሰደዱ ይታወቃል፡፡ የሀገራችንና የህንድ ሀገር ወጣቶችም እንዲሁ ወደ ዓረብ ሀገሮች ይሰደዳሉ፡፡ ሁሉም 2ኛ ደረጃ ት/ት አጠናቀዋል ቢባልም ከአገራችን የሚሄዱት ሴቶችና ከኤስያ የሚመጡት እኩያቻቸው የሚያገኙት የስራ አይነትና የክፍያ ሁኔታ የሚመጣጠን አይደለም፡፡ የኛዎቹ ሴቶች የግለሰብ ቤት ሰራተኛ ሆነው የኤሲያዎቹ ሴቶች ደግሞ በድረጅቶች ተቀጥረው ይሰራሉ፡፡የወንዶቹም ሁኔታ ቢሆን ከዚህ ብዙም የሚለይ አይደለም፡፡ የልይነቱ ምስጢር የኤሲያዎቹ ወጣቶች ወንዝ የሚያሻግር እውቀትና ስልጠና መያዛቸው ብቻ ነው፡፡

ወንዝ የሚያሻግር ችሎታና እውቀት መያዝ ብቻውን ኣይበቃም፤ ከዚህ በተጨማሪ የኣስተሳሰብ አድማሳቸው በክልል የታጠረ ሳይሆን ኢትዮጵያን በሙሉ የሚያካልል ካስፈለገም ከዚያ ባሻገር ወደ ውጪ አለም ተሻግሮ በማለፍ ሰርቶ ለመኖር የሚያስችል ሊሆን ይገባል፡፡

ዘመኑ አለም የተቀራበበት /የግሎባለይዜሽን/ ዘመን ነው፡፡ ስራ አለም አቀፋዊ ገፅታ እየያዘ የቅጥር ገበያም እንዲሁ ግሎባል እየሆነ በመሄድ ላይ በመሆኑ የሚሰጣቸው ትምህርት ስልጠና በአለምአቀፍ የሞያ ገበያ ላይ ተወዳድሮ ዋጋ ሊያወጣ የሚችል ሊሆን ይገባል፡፡የአገራችን ወጣቶች ከክልል አጥር የሚሻገር አመለካከት ብሎም የአለም ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪና ተመራጭ የምትሆኑት ለውድድር በቂ ሊያደርጋችሁ የሚችል እውቅትና ችሎታ ካገኛችሁ ብቻ ነው፡፡በዚህም ነው ኑሮአችሁን በስኬት አሸንፋችሁ ለማደር የምትችሉት፡፡

መድረክ ይህንን የሚቀይር ፖሊሲ አለው ፡፡ በአሁኑ ወቅት የሚያጋጥሟችሁን ፈተና ለመመለስ የምታደርጉት ጥረት የማን ድጋፍ ተመራጭ እንደሆነ መርምሩ፡፡ የሚሻችሁንም ምረጡ፡፡

**ከቡራን እና ከቡራት የመቀሌ ነዋሪዎች**

እኔ ንግግሬን ልቋጭ

እኔ ነፃነቴን አግኝቼ ከፊታችሁ ለመቆም በበቃሁበት በዚህ ወቅት የዛሬ 9 ዓመት እውነታንና የህግን መርሆች በመከተል ፍትህ የበየነችልኝ ዳኛ ወ/ሪት ብርቱኳን ሚደቅሳ ነፃነቷዋ ተገፎ ውህኒ ቤት ትገኛለች፡፡ በፖለቲካ አቋሟ ምክንያት ብርቱኳን ላይ የተቆለፈው የነፃነት በር ሊከፈት ይገባል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ብርቱኳን ትፈታ ብለን በጋራ እንድንጠይቅ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

ብርቱኳን የፓርቲ ለቀመንበር ለመሆን የበቃች የመጀመሪያዋ ሴት ፖለቲከኛ ነች፡፡ ለሴቶች መብት መቆም ማለት እንደ ብርቱኳን ና አረጋሽ የመሳሰሉት ገዢውን ፓርቲ ተቃውመውም ጭምር ወደ ፖለቲካ መድርከ ለሚመጡ ሴቶች ድጋፍ መስጠት ማለትም ነው፡፡ በመሆኑም ለፍትህና ለሙብቶች መከበር የምንታገል ዜጎች ሁሉ በተለይ ደግሞ ሴቶች ለብርቱኳን ነፃነት በኣንድነት መቆም ይገባናል፡፡

በመካከላችን የብሄር ወይም የፖለቲካ ልዩነት ሊኖር ቢችልም ሁላችንም ሰዎች ነን ፣ ሁላችንም ኢትዮጵያዊያን ነን ኢትዮጵዊነታችን የሁላችንም እጣ ፈንታ የተሳሰረ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም የፖለቲካ አቋሙ ምንም ይሁን፤ ብሄሩ ምንም ይሁን፤ ምን በማንም ኢትዮጵዊ ላይ የሚፈፀም በደል በእያንዳንዳችን ላይ እንደተፈፀመ ቆጥረን ግፍና በደልን በተገኘበት ሁሉ ልንታገለው ይገባል፡፡

በተለይ እኛ የትግራይ ተወላጆች ህወሓት /ኢህአደግ/ የሚፈፅማቸውን በደሎች በሚመለከት የራሳችን ነፃ ፣ ፍትህንና ፍትሃዊነትን መሰረት ያደረገ አመለካከትና አቋም ያለን መሆኑን ለኢትዮጵዊያን ወገኖቻችንና ለአለም ማ/ሰብ መግለፅ እንደሚያስፈልግ ልንገነዘብ ይገባል፡፡

አደራቸውን ትከሻችን ላይ አኑረው ለሄዱትና የሃይል አገዛዝን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድ ሲባል ለወደቁት የአገራችን ሰማዕታት በሙሉ ዘለአለማዊ ክብር ይገባቸዋል፡፡

# አመሰገናለሁ!!!